# መጻሕፍተ ሰሎሞን
# ወሲራክ

የጥበብ መጀመሪያ
እግዚአብሔርን
መፍራት ነው ።

## ዘውእቶን

- ምሳሌያተ ሰሎሞን
- ተግሣጸ ሰሎሞን
- ጥበበ ሰሎሞን
- መጽሐፈ መክብብ
- መኃልየ ሰሎሞን
- መጽሐፈ ሲራክ ዘኢያሱ

ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው

ንባቡና ትርጓሜው (በአንድምታ)

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ በሆኑ በ፩ኛው ዓመት ለ፪ኛ ጊዜ ታተመ ።

**<u>አሳታሚ</u>** ፦

ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
አ.አ. ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

__መግለጫ፡—__

ጌታ በወንጌል ፡— "እስመ ኢኮንክሙ አንትሙ ዘትትናገሩ አላ መንፈሱ ለአቡክሙ ሰማያዊ ውእቱ ይትናገር በላዕሌክሙ" (ማቴ· 10፥20) ሲል እንደተናገረው ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፉ በመሆናቸው "መጻሕፍት አምላካውያት" ይባላሉ ። (ፍት·ነገ·አን·2) እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ ሐዲሳት ቁጥር 81 ሲሆን መጻሕፍተ ብሉያቱ 46 ፤ መጻሕፍተ ሐዲሳቱ ደግሞ 35 በድምሩ 81 ናቸው ።

በየዐረፍተ ዘመኑ የተነሱት አበው ሊቃውንት መጻሕፍተ ብሉያትን ፤ መጻሕፍተ ሐዲስትንና መጻሕፍተ ሊቃውንትን ከዕብራይስጥ ፣ ከጽርእና ከአረቢክ ለሰው እንደሚገባ ፤ በምሥጢር ፣ በታሪክ ፣ በሐተታና በምሳሌ እየገላለጡ ፤ እያብራሩና እያፍታቱ ተርጉመውልናል ። ቢሆንም የመጻሕፍቱ ንባባቸውና ትርጓሜያቸው እጅግ በጣም ብዙ ሲሆን ፣ እንደ ዛሬም ሁሉ ወረቀትና የኅትመት መኪና ስለአልነበረ የመጻሕፍቱን ትርጓሜ የሚያጠኑና የሚያውቁ እጅግ በጣም ጥቂቶች ነበሩ ። የሚገኙትም በታላላቁ ከተሞች ፤ አድባራትና ገደማት ብቻ ነበር ። በዚህ ምክንያት አንድ ደቀ መዝሙር የብሉያትን ፤ የሐዲሳትንና የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ለመማር ከትውልድ አካባቢ መራቅ ፣ ከዘመድ መለየት ፣ የእድሜን እኩሌታ በትምህርት ማሳለፍ ግድ ነበር ።

ይህን ሁሉ ችግር አይተው ፣ ሊቀጥል የማይገባው መሆኑን ተገንዝበው ፤ በሚያስተምርና በሚማር እጦት የመጻሕፍቱ ትርጓሜ እንዳይጠፋ ፤ የሚማሩትም ሆነ የሚያስተምሩት ደቀ መዛሙርትና መምህራን ችግር እንዲቃለል ፤ ሙያውና እውቀቱም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ፤ ማንኛውም ሰው የመጻሕፍትን ምሥጢር እንዲረዳ ለማድረግ የአርቆ ተመልካችነት እድል ከልዑል እግዚአብሔር የተሰጣቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን ሊቃውንቱን ከያሉበት ሰብስበው የመጻሕፍትን ንባባቸውንና ትርጓሜያቸውን አጽፈው ፣ በ፲፱፻፲፩ ዓ·ም· የኅትመት መኪና ከአውሮፓ አስመጥተው በአንድምታ ከአሳተሙአቸው መጻሕፍተ ብሉያተ ውስጥ ፦

1ኛ· ምሳሌያተ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ፤

2ኛ· ተግሣጽ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ፤

3ኛ· ጥበበ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ፤

4ኛ· መጽሐፈ ሰሎሞን መክብብ ፤

5ኛ· መኃልየ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ፤

6ኛ· መጽሐፈ ሲራክ ዘኢያሱ ናቸው ። እነዚህ መጻሕፍት የታተሙት በ፲፱፻፲፯ ዓ·ም· ሲሆን ከዚያን ጊዜ እስከአሁን እነሆ ! ፸፩ ዓመታት መሆናቸው ነው ።

ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባውና ሊቃውንት አባቶቻችን "ቅድመ መሀርዎሙ ለውሉድክሙ መጽሐፈ ሰሎሞን ወሲራክ ወመዝሙረ ዳዊት " ሲሉ እንዳቆዩትና እንዳስተማሩት ለሚማሩትና ለሚያስተምሩት ፤ ሙያውን ለሚሹት ሁሉ ጥንት ከነበረው ሳይቀነስ ሳይጨመር እንዳለ ለ፪ኛ ጊዜ ቋሳትመን ስናቀርብ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል

የማሳተሚያ ድርጅቱ ኃላፊ።

፲፱፻፹፰ ዓ·ም·



ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

# ማውጫ


የመጻሕፍት ብሉያት ታሪክ .................... I

ምሳሌያተ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት .................... ፲

ተግሣጸ – ሰሎሞን ወልደ ዳዊት .................... ፺፯

ጥበበ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት .................... ፻፭

መጽሐፈ ሰሎሞን መክብብ .................... ፻፳፭

መኃልየ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት .................... ፻፺፯

መጽሐፈ ሲራክ .................... ፪፻፴፭

ልክን አ ነግሦ ከሄኖክ እሱ እስከ ጻፋቸው ያሉትን መጻሕፍት ሰብስቦ እነዚህንም መጻሕፍት ተርጕመው የሚያስተምሩ ፫፻ ፲፰ ሌዋውያንን ጨምሮ ሰጥቶ ሰደደው ። እነሱም መጥተው መጻሕፍተ ብሉያትን ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ መልሰው አስተምረዋል ።

ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ እንደ ተመለሱም የሚያስረዳ ነገር በተለየ ለኛ መጀመሪያ በተመለሰልን በመጽሐፈ ነገሥት አዶናይ ኤሎሄ ጸባዖት እያለ የእብራይስጡን ቋንቋ ጽፎ ይገኛል ።

ይህነንም አባ ጊዮርጊስ ከጻፋት ከታሪክ መሐጽፍ አምጥተን ከዚህ ቀጥለን በምንጽፈው እናሳያለን ።

ወመክብበ መጻሕፍቲሆሙሰ ዘብሉይ ተቀበልዋ ። እምእብራይስጢ ኀበ ግዕዝ በመዋዕሊሃ ለንግሥተ አዜብ እንተ ሖወጸቶ ለሰሎሞን ። ወበእንተዝ ኮነ ጽሑዮ ፍካሬሆሙ ለመጻሕፍተ ነቢያት ዘውስተ ብሔረ አግዐዚ ። እስመ በሕገ `አይሁድ ነበሩ ። እምቅድመ ልደተ ክርስቶስ ። ወእመሰኬ አዕለውዎ እምድኅረ ልደተ ክርስቶስ እሜጡ ሰቃልያን ቃለ ጽድቅ ውስተ ስምዓ ሐሰት ከመሰ ተዓልዋ መጻሕፍተ ነቢያት እምእብራይስጢ ኀበ ግዕዝ ትረክብ ትእምርተ በመጽፈ ነገሥት ዘይብል ትርጓሜ ነገረ እብራይስጢ ኀበ ግዕዝ ኤሎሄ ብሂል አምላክ አዶናይ ብሂል እግዚእ ጸባዖት ብሂል ዘኃይላት ይላል ።

ሁለተኛ ፤ ከቀውስጦስ ታሪክ መጽሐፍ ምሥክር እናመጣለን በ፬ ሽህ ፱፻፫ ዓመተ ዓለም እስራኤል ተማርከው ፋርስ ባቢሎን ወረዱ ። ተማርከው ከሄዱ በኋላ በኢትዮጵያ ያሉ ሊቃውንት ከንጉሡ ጋራ መክረው የጥያቄ መልእክት ላኩ ። ነገሩም እንዲህ ነው ፤ የኛም የናንተም አባቶች ነቢያት የጻፏቸው መጻሕፍት ተቃጠሉን ወይስ ድነዋል እናንተስ እንደምን አላችሁ ለጣዖት ትሰግዳላችሁን ሰንበትንስ ሻራችሁን የሚል ነው ። እነዚያም ይህን መልእክት በሰሙ ጊዜ እንዲህ ብለው መልሰዋል እኛ በነዳንኤል ጸሎት የአብርሃም ፈጣሪ ጠብቆን ደህና ነን መጻሕፍቱን ግን እኛ እንዳንፈልጋቸው በምርኮ በመከራ ነው ያለን እናንተ ግን በጸጥታ በደስታ ነውና ያላችሁት ኢየሩሳሌም ወጥታችሁ ፈልጓቸው ፤ ነገር ግን ከተማረክን በኋላ ዳንኤል ከእግዚአብሔር አግኝቶ የጻፈውን መጽሐፍ ጽፈን ልከንላችኋልና ተቀበሉ ብለው መጽሐፈ ዳንኤል ልከውላቸዋል ። ይህም መጽሐፍ የመጣ አይሹር የሚባል የኢትዮጵያ ንጉሥ ስለ ዘመዶቹ ስለ እስራኤል ወደ ፋርስ ንጉሥ ወደ ዳርዮስ አማላጅነት በላከው ሰው እጅ ነው ። ይህነንም መጽሐፈ ዳንኤልን ተቀብለው በሰሎሞን ጊዜ ካባቶቻችን ጋራ ከመጡ መጻሕፍት ደርበውታል ።

ከዚህ በኋላ በአራት ሽህ ፱፻ ፸፫ ዓመተ ዓለም እስራኤል ከተማረኩበት ከባቢሎን ወደ አገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። በዚህ ጊዜ ዘሩባቤል ነገሠ ። ከዚህ በኋላ ዘሩባቤል ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ እንዲህ ሲል ላከ ፤ ሰላም ላንተ ይሁንና ስለ እግዚአብሔር ብለህ የለመንኩህን ስማኝ ፤ ከኢየሩሳሌም ጥፋት አስቀድሞ ነቢያት የጻፏቸው መጻሕፍት ፤ በአያትህ በሰሎሞን ልጅ በምኒልክ መንግሥት መጥተው ባገርህ አሉና ጽፈህ ላክልኝ ብዬ ባባቶቻችን ፈጣሪ በክበረ ስሙ እማልድሃለሁ ። እኔም ወደ እናንተ ያልመጡትን ከኛ ዘንድ ያሉትን መጻሕፍት እልክልሃለሁ ፤ ይህ ላንተም ለኔም ደግ ነው ብሎ ላከ ፤ የኢትዮጵያ ንጉሥም የዘሩባቤልን መልእክት በሰማ ጊዜ ካህናቱን ጠርቶ በሀገራችን ያሉ መጻሕፍተ ነቢያትን ይዛችሁ ኢየሩሳሌም ሂዱና ለዘሩባቤል ስጡ ። እናንተም ቀድሞ በአባቶቻችን ዘመን ያልመጡት መጻሕፍተ ነቢያትን ጽፋችሁ አምጡ ብሎ ሁለት ሽህ ወቄት ወርቅ ለስንቃቸው ። ሁለት መቶ ወቄት ወርቅ ለንጉሥ እጅ መንሻ ሰጥቶ ሰደዳቸው ።

እነሱም መጻሕፍቱን እጅ መንሻውንም ይዘው ሂደው ለንጉሡ ሰጥተው በዘመኑ ካሉ ከደቂቀ ነቢያት ተገናኝተው ወደኛ ያልመጡትን መጻሕፍት ጽፈው ይዘው ተመልሰዋል ። እንዲያውም የኢትዮጵያ ሰዎች በምኒልክ ጊዜ መጻሕፍተ ነቢያት ከተመለሱላቸው ወዲህ በአሪቱ ሥርዓት እጅ

ሊነሡ መባዕ ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም ለበዓል ይ
ወጡ ነበር ። በኢዮስያስ ዘመን የተነሣ ከሥራ ሁለ
ቱ ደቂቀ ነቢያት አንዱ ሶፎንያስ ም ፫ ቍ ፲ ከ
ኢትዮጵያ ወንዝ ማዶ የሚሰግዱልኝ የተበተኑት
ልጆቼ መባዬን ይዘው ይመጣሉ ብሎ እንደ ተናገ
ረ ይህም በኢትዮጵያ ሕገ ኦሪት መኖሩን ያስረዳል

ሶስተኛ ፤ በአምስት ሽህ ሁለት መቶ ዓርባ አ
ምስት ዓመተ ዓለም በጥሊሞስ ንጉሥ ይኸውም ከ
እስክንድር ሶስተኛ መንግሥት ነው ። መጻሕፍተ ነ
ቢያት ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ እንደ ተመለሱ በ
ሁሉ ታውቋልና እሱም ይህን ይዘ ጸሐፍቱንም
መጻሕፍቱንም ስደዱልኝ ብሎ በኢየሩሳሌም ወደ
አሉ አይሁድ ላከ እነሱም ሰደዱለት በዚህ ጊዜ
መጻሕፍተ ነቢያት ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ ተመል
ሰውላቸዋል ።

ዓራተኛ ፤ ፊት እንደ ተናገርነው የኢትዮጵያ
ሰዎች በኦሪት ሕግ አምነው በኢየሩሳሌም ሊሰግዱ
ይወጡ እንደ ነበርና ከክርስቶስ ልደት በፊት መ
ጻሕፍተ ነቢያት ወደ ግዕዝ ተመልሰው በኢትዮጵ
ያ ተሰብስበው እንደ ነበር የሚያስረዳ ነገር በሐዋ
ርያት ሥራ ተጽፎ እናያለን የሐ ሥራ ፰ ፳፯ ፵
ድረስ ተመልከት። ከጌታችን ዕርገት በኋላ ፤ የኢትዮ
ጵያ ንግሥት የሕንደኬ ጃንደረባ የሚሆን አንድ የ
ኢትዮጵያ ሰው በኦሪት እንደ ታዘዘው ሥርዓት
ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። ሰግዶም ተመልሶ
በሠረገላ ተቀምጦ መጽሐፈ ኢሳይያስ እየደገመ
ሲሄድ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ተከተለው አለው
ፊልጶስም ተከትሎ ቢሰማው መጽሐፈ ኢሳይያስ
በቋንቋው በግዕዝ ሲደግም ሰማው ከዕርገት በኋላ
በአሥረኛው ቀን ብዙ ቋንቋ ተገልጾላቸዋልና ሰ
ማው ( የሐ ሥራ ፰ ፴፪) የሚደግመውም አንቀጽ
ከመ በግዕ መጽአ ይጠባሕ ወከመ በግዕ በቅድመ
ዘይቀርጾ ከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ ወተን
ሥአ እምኵነኔ ወእሞቅሕ ወመኑ ይነግር ልደቶ
እስመ ተአተተ እምድር ሕይወቱ ። የሚለውን ነበ
ር ኢሳ ፶፫ ፯ ( ፊልጶስም ይህን የምትደግመውን
ምሥጢሩን ታውቀዋለኽን አለው ያም የኢትዮጵ
ያ ሰው መጻሕፍተ ነቢያትን ጠንቅቆ ተምሯልና የ
ተማረውን ደገመ እንጂ ትንቢቱ እንደ ደረሰ ም
ሳሌው እንደተፈጸመ አያውቅምና እኔ ያስተማረኝ
ሳይኖር እንደምን ማወቅ ይቻለኛል ነገር ግን ነቢይ
ይኸን የተናገረ ስለ ራሱ ወይም ስለ ሌላ እንደሆ
ነ ንገረኝ ብሎ ፊልጶስን ለመነው ፊልጶስም በዚሁ
መጽሐፍ የኢየሱስን ነገር አስረድቶ አጥምቆታል
ያም የኢትዮጵያ ሰው ደስ እያለው ወደ አገሩ ተ
መልሷል። ይኸንንም በሐዋርያት ስራ የተጻፈውን
ቃል የስንፍና እርካብ ተረግጦ ባለ መመርመር ፈ
ረስ ተቀምጦ ፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በኢትዮጵያ
መጻሕፍተ ብሉያት በግዕዝ አልተሰበኩም ማለት የ
ሕልም ሩጫ ይባላል ነገር ግን ከሚጠራጠር በቀር
ለሚያስተውል ሰው ይህ ብቻ ያስረዳል ።

ጥንቱን ሌዋውያን ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ
መልሰው መጻሕፍተ ነቢያትን ያላስተማሩ ቢሆን
ይህ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም
እንደምን ይሄድ ነበር ዳግመኛስ በፊት እንደተና
ገርነው በአይሹር ወይም በአይዙር ዘመን መ
ጻሕፍተ ነቢያት ካልመጡልን ይህ የኢትዮጵያ ን
ግሥት ጃንደረባ መጽሐፈ ኢሳይያስን እንደምን
ያውቅ ነበር ፡ ካላወቀስ እንደምን ያነብ ነበር ቅዱ
ስ ጳውሎስ እንዲህ ይላልና ወባሕቱ እፎ ይጼው
እዎ እንዘ ኢየአምኑ ቦቱ ወእፎ የአምኑ በዘኢ
ሰምዑ ወእፎ ይሰምዑ ዘኢሰበኩ ሎሙ ወእፎ ይሰ
ብኩ ሎሙ ዘኢተፈነወ ሐዋርያ ኀቤሆሙ ብሏልና ።
ሮሜ ፲ ፲፬ ።

ሁለተኛ ፤ ንግሥተ አዜብ ወደሰሎሞን በሄ
ደች ጊዜ ጋዛ ላይ ሠፍራ ነበርና ስትመለስ ጕ
ልት ይሁኝሽ ብሎ ስለሰጣት አንዳንድ ጠባቂ ሹ
ም ይቀመጥበት ነበር ። ይኸም የኢትዮጵያ ንግሥት
ጃንደረባ በዚያው ልማድ ተሹሞ በጋዛ የሚኖር
ኢትዮጵያዊ ነው የሚል ሰው ቢኖር ሰሎሞን ለን
ግሥተ አዜብ ጕልት ይሁንሽ ብሎ ጋዛን እንደ ሰ
ጣት ጠባቂም እንድታደርግበት በሌላም ታሪክ
ሁሉ የተገለጠ ነገር ነው ። ፩ ነገሥት ፲ ፫ ይልቁ
ንም ንጉሡ ሰሎሞን ለሳባ ንግሥት የወደደችውን
ሁሉ ከርሱም የለመነችውን ሁሉ ሰጣት ተብሎ
የተጻፈው ቃል የስጦታውን ነገር በጣም ያስረዳል

ጻፉ ግን ይህ ሕፅው በጋዛ ተሹሞ የሚኖር መሆኑን ። በሐ ሥራ ፰ ፳፯ ። የተጻፈው ቃል እያስረዳም በኢየሩሳሌም ሊሰግድ ከኢትዮጵያ የሄደ መሆኑን እንጂ በጋዛ ተሹሞ የሚኖርስ ቢሆን ያስተማረኝ የሌለ እኔ ማወቅ እንደምን ይቻለኛል ባላለም ነበር። የሐዋርያት ነገራቸው በአራቱ ማዕዘን ተሰምቷል ትምሕርታቸውም ጽንፍ እስከ ጽንፍ ደርሷልና ። መዝ ፲፰ ፬ ሮሜ ፲ ፲፰ ። በግዕዝ የተጻፉ የሀገራችን መጻሕፍተ ብሉያት ጥንታቸው መሠረታቸው እብራይስጥ እንደሆነ የመለሱዋቸውም ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሌዋውያን እንደሆኑ በትክክል ከሚያስረዱ መጻሕፍት አውጥተን እነሆ ጽፈናል ። ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ከአባቶቻችን ያገኘነው ታሪክ ይህ ነው ይልቁንም ዛሬ ወፈድፋደ ጸንቶ እምቀደምቶሙ ይላልና የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈሪ ። በ፲፱፻፲፪ ። ዓመተ ምሕረት ሁላችሁም በቋንቋ ትናገሩ ዘንድ እወዳለሁ ይልቁንም ትተረጒሙ ዘንድ በቋንቋ ከሚናገር የሚተረጒም ይበልጣልና ያለውን ተመልክተው ። ፩ ቆሮ ፲፬ ፭ ። አባቶቻቸው በንባብ ከቋንቋ ወደቋንቋ የመለሱዋቸው ብሉያትንና ሐዲሳትን ሊቃውንትንና መጽሐፈ መነኮሳትን እሊህን አራቱን ጉባኤያት ንባባቸውን እስከ ትርጓሜያቸው አሳትመው የኢትዮጵያን ሰው ሁሉ ወደ እውቀት ጎዳና መርተው ሁሉም በየቤቱ እንክሰ ኢንፈቅድ መርሃ ገላ ፫ ፳፰ ። እስመ ኵልነ ውሉደ ብርሃን ። ተሰሎ ፭ ፭። እያለ ፈጣሪውን እንዲያምንና እንዲያመሠግን አደረጉት ። የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንንን አነሣሥቶ የቅዱሳት መጻሕፍት ንባባቸው እስከ ትርጓሜያቸው እንዲጻፍ ያደረገ እግዚአብሔር ይክበር ይመሥገን ። አ ሜ ን ።

